መሪ ርዕስ ፡- “እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ” ሐዋ.13፥22

# የዳዊት ሕይወት ከእረኛነት እስከ ንግስና

## የአካባቢ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

**በሚቀጥሉት ተከታታይ ጥናቶች የንጉስ ዳዊትን ህይወት እናጠናለን።**

## ጥናት 1

**ርዕስ፡- የተቀባው እረ 1ሳሙ.16፥1-13**

**ዓላማ፥**

- **እግዚአብሔር የሚመርጣቸውና ኃይሉን የሚያሳይባቸው ሰዎች በሰው ዘንድ ያልታሰቡና እንደውም የተናቁ እንደሆኑ ለማሳየት**

- **እግዚአብሔር ሰውን ለስራው ሲመርጥ ፊትን ሳይሆን ልብን እንደሚያይ ለማስገንዘብ**

**መግቢያ፥**

**እስራኤላውያን በፊታችን የሚሄድ ከጠላቶቻችን የሚያድነን ንጉስ ቀባልን ብለው እግዚአብሔርን ጠይቀው ነበር። እግዚአብሔርም የንጉስን ሥርዓት ቢነግራቸውም ሥርዓቱ አይሁን ነገር ግን ንጉሥ አንግሥልን አሉት። እግዚአብሔር የቀባላቸው ንጉስ ግን ለእግዚአብሔርና ለህዝቡ የማይመች ሆኖ ስለተገ እግዚአብሔር የወሰደውን እርምጃ እናያለን።**



2

3. እግዚአብሔር ለዳዊት ያደረገለት ምንድነው? "በፊቴ ገበታን አዘጋ- ህልኝ" እና "ጽዋዬ የተረፈ ነው" ከሚሉት ሃረጎች ምን ትረዳለህ? እንዴት ይገና ሉ?
4. ዳዊት በእግዚአብሔር ቤት ለዘላለም እንደሚኖር በድፍረት የሚናገረው ከምን የተነሳ ነው?
   - "ቸርነትህና ምህረትህ በህይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉ ል የሚለው ሃሳብ ከአጠቃላይ ክፍሉ ጋር እንዴት ይያያዛል?

<u>ተዛምዶ</u>

- እረ ህን እግዚአብሔርን ምን ያህል ተረድተከዋል?
- አንተስ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለመጠበቅ የምትተማመንባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
- እግዚአብሔር በሚያሰማራህ ሥፍራ ሁሉ ለመሰማራት ምን ያህል ፈቃደ ነህ?
- ከክፍሉ ለግልህ የተማርከውን አዲስ ነገር ካለ አካፍል



መሪ ርዕስ ፡- "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.13፥22

<u>ጥያቄዎች፥</u>

1. በክፍሉ መ- መሪያ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለሳሙኤል ምን ነበር? ለምን ይህን አደረገ?
2. እግዚአብሔር ሳኦልን እንዳይነግሥ የናቀበት ምክንያት ምንድን ነበር? ምዕ 15፥22-23
   -- ሳኦል ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረት ሳያገኝ ቀረ?
3. እግዚአብሔር ለሰጠው ትዕዛዝ የሳሙኤል መልስ እንዴት ነበር?
   -- እግዚአብሔር ምን አይነት መንገድ እንዲጠቀም ሲነግረው ይታያል?
4. ሳሙኤል ወደ ቤቴልሄም በመጣ ጊዜ የህዝቡ አቀባበልና እርሱስ ያደረገው ነገር ምን ነበር?
   -- ወደ መስዋዕቱ ለጠራቸው ለእሴይ ቤት ምን ሲያደርግ ይታያል?
5. ሳሙኤል ኤልያብን ባያ ጊዜ የህዝቡ አቀባበልና እርሱስ ያደረገው ነገር ምን ነበር?
   -- ለምን የእግዚአብሔርና የሰው ምርጫ ተለያየ ትላለህ?
6. በተናቀው ንጉሥ ምትክ እግዚአብሔር ስለመረጠው ሰው ማንነት ምን ይናገራል?
   -- የመቀባቱ ውጤት ምን ነበር?
   -- የተቀበለው መንፈስ ከዚህ በኋላ ለሚኖረው ህይወት ያለው ድርሻ ምንድነው?

7. በሰው ዘንድ የተረሳ የሆነውንና ቅን ልቡና የነበረውን ሰው እግዚአብሔር እንደዚህ አድርጎ እንደቀባው ስትመለከት በእግዚአብሔር ላይ ልብህ ለመደገፍ ምን ያህል ጽኑ ነው?

– እግዚአብሔር የሚመርጣቸው ሰዎች ምን ዓይነት ናቸው? የተቀበለው መንፈስ ለተሰጠው አገልግሎቱም ሆነ ቦታ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ቅባት ትፈልጋለህ?



መሪ ርዕስ ፡- "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.13፡22

## ጥናት 14

**ርዕስ፥ እረ ውን የተረዳው ዳዊት መዝ.23፡1-6**

ዓላማ፥ አማኝ እረ ውን እግዚአብሔርን በሚገባ ለይቶ ማወቅ እንዳለበትና በእግዚአብሔር እረኝነት ስር ያሉት በሙሉ እግዚአብሔርን በመተማመን የበረከቱ ተካፋዮች እንደሚሆኑ ለማሳየት

መግቢያ፥እግዚአብሔር እረ ው የሆነለት ዳዊት እግዚአብሔር እንዴት ያሰማራው እንደነበር እንመለከታለን።

ጥያቄዎች፥

1. ከቁ.1-4 ዳዊት ስለ እግዝአብሔር እረኝነት ምን ይዘረዝራል?

   - እግዚአብሔር ዳዊትን ያሰማራው የነበረው በምን አይነት ቦታና መንገድ ነው?

   - እግዚአብሔር እረ ዬ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው? ነፍሴን መለሳት ሲልስ?

2. የእግዚአብሔር ከዳዊት ጋር መሆን በዳዊት ህይወት ያስከተለው ውጤት ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

   - ስለ በትርና ምርኩዝ አገልግሎት ዘርዝር። እነዚህስ እንዴት ያጽናናሉ?

“አንተ ፊቴን እሹት ባልህ ጊዜ…” ሰቐቆ የእግዚአብሔርን ፊት መቼ ነው መፈለግ ያለብን?

6. በቁ.13,14 የሚናገረው ከላይ ከጸለየው ጸሎት ጋር እንዴት ይዛመዳል?

- በተስፋ መጠበቅና የልብ ጽናት እንዴት ታያይዘዋልህ?

ተዛምደ

- በእግዚአብሔር የሚታመን ህይወትህን ስትመዝነው እንዴት ሆኖ አገ ከው
- በእግዚአብሔር ከመታመንህ የተነሳ ምን ያህል ከፍርሃትና ከድንጋጤ ነጻ ሆነህ ትኖራለህ?
- በእግዚአብሔር ሊደረግልህ የምትወደው የመ- መሪያ ጥያቄህ ምንድነው?
- የሚያስፈራና የሚያናውጥ ፈተና ህይወትህን ሲገጥማት በጌታ ላይ የሚኖርህ እምነትና ትምክህት ምን አይነት ሆኖ ታገ ዋለህ?
- የዚህንስ አመለካከት ጥቅሙንና ጉዳቱን መስክ
- አስቸጋሪ ፈተናና መከራ ሲያጋጥምህ ከጌታ ጋር ለሚኖረው የህይወት ጽናትና ጤናማ ግን ኑነት አስቀድሞ መጸለይ ፈተናውን በድል ለማለፍ የሚኖረው አስተዋጽዖ ምን እንደሆነ ተረዳህ?



መሪ ርዕስ ፡- “እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ” ሐዋ.13፥22

## ጥናት 2

## ርዕስ ፥ በወንጭፍና በድንጋይ ያሸነፈው እረ

## 1ሳሙ.17፥31-54

ዓላማ ፥ አማኝ በጠላቱ ላይ ድል መንሳቱን የሚገ ው በእስራኤል አምልክ በእግዚአብሔር ስም በመታመኑ እንደሆነ ለመሳየት

መግቢያ፥ ከእረኝነት ለንጉስነት የተቀባው ንጉስ በፍርሃትና በጠላት ጥቃተ ውስጥ የነበሩትን እስራኤላውያን እንዴት ጠላታቸውን ተዋግቶ እንዳሸነፈ እናያለን

ጥያቄዎች፥

1. በዚህ የሰልፍ ጊዜ የዳዊትና የሳያልን ንግግር ምን ነበር?
   - ዳዊት ይህንን ፍልስጤማዊ ለመግጠም እንደሚችል ሲናገር ሳያል ዳዊት ጎልያድን መግጠም እንደማይችል ያቀረበው ምክንያት ምን ነበር?
2. ዳዊት ጎልያድን መግጠምና ማሸነፍ እንደሚችል ሲናገር የሚያቀርበው ማስረጃ ምንድነው ነው?
   - በዚህ የሰልፍ ሜዳ ዳዊት የሚተማመንበት ነገር ምን እንደሆነ ታያለህ?

3. ሳዖል ለዳዊት ምን አይነት መልስ ሲሰጠውና ሲያደርግ ይታያል?

   - ሳዖል የሰጠውን ትጥቅ ዳዊት ለመተው ምክንያት የሆነው ነገር ምንድነው?

   - ሳዖል በሰጠው ትጥቅ ፈንታ ዳዊት ወደ ፍልሚያው ቦታ ይዞት የሄደው ምን ነበር?
4. ሁለቱን የውጊያ መሳሪያዎች አወዳድር
5. በሰልፉ ሜዳ ላይ ጎልያድ ዳዊትን ምን ሲለው ይታያል? የዳዊትስ ምላሽ ምን ነበር?
6. ሁለቱ ተጋጣሚዎች የያዙትን መሳሪያ አወዳድረህ ስትመለከት እያንዳንዳቸው አንዱ ሌላውን እንዲያሸንፍ ብቁ የሚያደርጋቸው ነገር ምን እንደሆነ ይናገራሉ?
7. በዳዊት አነጋገር የሰልፉ ውጤት ምን እንደሆነ ነው የሚናገረው? - አስቀድሞ በአባቱና በሳሙኤል አሁን ደግሞ በጎልያድ ተንቆ የነበረው ዳዊት እንዲህ ያለ ማሸነፍ ማድረጉን ስታይ ስለ እግዚአብሔር አሰራር ምን ትረዳለህ?
8. ዛሬስ በግል ህይወትህ ምን አይነት ውጊያ አለብህ? በዚህስ ድል ለማድረግ ምን ያህል ትተጋለህ?

   - በጠላቶቻቸው ፊት አፍረውና ተዋርደው ለነበሩት እስራኤላውያን ዳዊት ቀንቶ ያደረገው ነገር ስትመለከት አንተስ በጠላት ጥቃተ ውስጥ ያሉትን ነጻ ለማድረግ ምን ማድረግ እንዳለብህ ታያለህ?



መሪ ርዕስ ፡- “እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ” ሐዋ.13፡22

## ጥናት 12

**ርዕስ፥ ልቡን በጌታው ላይ ያጸናው ዳዊት**

**1ዜና 21፡1-21**

ዓላማ፥ አማኝ በእግዚአብሔር ታዳጊነት ጥበቃ በመተማመን መኖር እንዳለበትና በመከራው ጊዜ የእግዚአብሔርን ፊት ሊፈልግ እንደሚገባው ለማስገንዘብ

መግቢያ፥ ዳዊት ጥልቅ በሆነ መንገድ ከእምነት ህይወት ጋር የተዛመደውን ሃሳብ በመዘርዘር የሚናገረውን ክፍል በዛሬው ጥናታችን እናያለን።

ጥያቄዎች፥

1. በመ- መሪያው ቁጥር ዳዊት ምን ይናገራል?
2. ከክፍሉ ሃሳብ ጋር ስታዛምድ “ብርሃንና መድሃኒት” የሚሉት ቃላትን እንዴት ትረዳለህ?
3. በክፍሉ ውስጥ ለዳዊት አስፈሪና አስደንጋጭ ተብለው የተዘረዘሩትን ነገሮች ምንድን ናቸው? - በእነዚህ ነገሮች ላለመፍራትና ላለ መደንገጥ ምክንያት የሆኑት ነገሮች ምን ምን ናቸው?
4. ዳዊት እግዚአብሔርን የሚጠይቀው ነገር ምንድን ነው? - ይህ ጸሎት /ቁ.4/ ከክፍሉ ሃሳብ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
5. ከቁ.7-12 ዳዊት የሚጸልየው ጸሎት ምንድነው?

4. እግዚአብሔር በጋድ በኩል ለዳዊት ስለ በደሉ ቅጣት አማራጭ ባኖረለት ጊዜ ያደረገው ምርጫ ምን ነበር? - ይህስ የምርጫው ሁኔታ ስለ ዳዊት ባህርይ ምን እንድታስተውል ያደርግሃል?

"በእግዚአብሔር እጅ ልውደቅ በሰው እጅ ግን አልውደቅ ከሚለው ሃሳብ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው እያወዳደርክ ተናገር።

5. በቁ. 17 ዳዊት ለእግዚአብሔር የተናገረው ነገር ምንድነው? - ይህስ ስለ ዳዊት ባህርይ ምን እንድታይ ያደርግሃል? ውጤቱስ?
6. ቁ.22-25 ስለ ኦርናን ዳዊት ምን ትመለከታለህ? - የአውድማውን ቦታ ለምን በነጻ አልተጠቀመበትም?
7. ዳዊት ስለ እግዚአብሔር የነበረው መረዳት /የእግዚአብሔር ምህረት/ በጥናት ክፍሉ ውስጥ እንዴት ተገልጾ አገ ከው? ቁ.15-17
8. እግዚአብሔር ምህረቱ ብዙ በመሆኑ በሰው ከመውደቅ ይልቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ እንደሚመረጥ ምን ያህል አስተዋልክ?

⌖ ስለምታገለግላቸው ሰዎች በኑሮ ውስጥ ባለው ችግርና መከራ ራስህን አሳልፈህ ለመስጠት ምን ያህል ፈቃደ ነህ? - እግዚአብሔር በቅንነት ለሚጠሩት በርኅራኄ የሚመልስ ለመሆኑ በግል ህይወትህ ምን ያህል ተለማምደከዋል? በግልህ የተማርከውን አዲስ ነገር ተናገር።



መሪ ርዕስ ፡- "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.13፥22

- ሌላ ከዚህ ክፍል ያስተዋልከውን ብታካፍለን?

## ጥናት 3

**ርዕስ፥ "በቀልን ለእግዚአብሔር የተወው ዳዊት"**

**1ሳሙ.24፥1-22**

ዓላማ፥ ዓማኝ እርሱን በክፉ የሚፈልጉትን ሰዎች ከመበቀል ይልቅ ለእግዚአብሔር መተው እንደሚገባው ለማሳየት

መግቢያ፥ ንጉስ ሊሆን የተቀባው እረ ው ዳዊት ከጎልያድ ጋር ተዋግቶ ካሸነፈ በኋላ ሳዖል ተመቅኝቶ ተመለከተው ስለዚህም በዳዊት ላይ ሊያደርግ የፈለገውን ነገር እናያለን።

ጥያቄዎች፥

1. ፍልስጤማውያንን ከማሳደድ ለተመለሰው ሳዖል ስለ ዳዊት ወሬኞች የነገሩት ነገር ምን ነበር? እርሱስ ምን ሲያደርግ ይታያል?
   - ከ 400 የማይበልጡትን የዳዊት ተከታዮች ከእነ ָህ ሶስት ሺህ ከሆኑና ከተመረጡ ሰራዊት እጅ የሚያመልጡ ይመስልሃልን? ለምን?
2. ዳዊትን ሊያጠፋ የፈለገው ሳዖል ያጋጠመው ነገር ምን ነበር?
   - ማስታዎሻ፥ ወገቡን ሲሞክር ማለት ሲጸዳዳ ማለት

ነው።

- የዳዊትና የተከታዮቹ ምላሽ ምን ነበር? በተጨማሪ ምዕራፍ 26፥6-12 ተመልከት

3. ይህንን ንጉስ በህዝቡ በእስራኤል ላይ እንዳይነግስ እግዚአብሔር ንቀት እንደነበር ዳዊት እያወቀ በሳዖል ላይ እጅ አለመዘርጋቱን ስትመለከት ምን ታስተውላለህ?
4. ሳዖል የሆነበትን ሁሉ ሳያውቅ ከዋሻው ከወጣ በኋላ ዳዊት በመጣራት የሚናገረው ነገር ምንድን ነው? - ከዚህ አነጋገሩ ስለ ዳዊት ባህርይ ምን ትረዳለህ? በተጨማሪ ምዕ.26፥7
5. ዳዊት ባለፈው ጥናታችን ለጎልያድ የመለሰለትንና አሁን ደግሞ ለሳዖል የሚያሳየውን ነገር በማወዳደር ስለ ዳዊት ባህርይ ተናገር?
6. የሳዖል ምላሽ ምን ነበር?

   - እግዚአብሔር ንጉስ አድርጎ በእስራኤል ላይ እንደቀባውና እንደሚነግስ ሲያጸናለተ እግዚአብሔር በጠላቱ በሳዖል በኩል መናገሩና ሳዖልም ማወቁ ሲታይ ዳዊት ከዚህ ሁኔታ ምን ያስተውላል?
7. አንተስ ክፉ ያደረገብህን እንደ ዳዊት እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፉ ቢሰጥህ ምን ታደርግበታለህ? ለምን?

   - በመስሪያ ቤትና በጎረቤት ባለህበት ስፍራን ሆን ብሎ አዘውትሮ አንተን ለማጥፋት የሚነሳብህ ሰው ቢያጋጥምህ ምን ታደርጋለህ?





## ጥናት 11

ርዕስ ፥ የዳዊት አስደናቂ ምርጫ 1ዜና. 21፥1-27

ዓላማ፥ 1. አማኝ የቱንም ያህል ቅን ሰው ቢሆን እንኳ ሊሳሳት እንደሚችልና ላደረገው ስህተት ሊያሳየው የሚገባውን የቅንነት ምቅሽ ለማሳየት

2. ከተሳሳቱ በኋላ ለስህተቱ እርጉት ማስተዋል ያለበትን ምርጫ ሊመርጥ እንደሚገባው ለማሳየት

መግቢያ፥ ዳዊት የእግዚአብሔር ህዝብ እንዲቆጠር በማድረጉ ያስከተለው ችግርና ለበደሉ ቅጣት እግዚአብሔር ላኖረቃት አማራጮች ያደረገውን ምርጫ እንመለከታለን።

ጥያቄዎች

1. ዳዊት ለኢዮአብና ለሕዝቡ አለቆች ምን እንዲያደርጉ ያዛቸዋል?

- ይህን እንዲያደርጉ የገፋፋው ምንድነው? ለምን ገፋፋው?

2. ለቆጠራው የኢዮአብ አመለካከት ምንድነው?
3. የዳዊት ህዝቡን መቁጠር ያስከተለው ችግር ምንድነው?

⌖ ህዝቡን መቁጠር ይህን ያህል መቅሰፍት ለምን ሊያመጣ ቻለ ትላለህ?

4. ዳዊት ከስደት ሲመለስ አቀባበል ምን የመስላል?
   - የይቅርታ አጢያየቁ ሁኔታስ?
5. አቢሣ አሁንስ ምን ርምጃ ለመውሰድ ያስባል? ዳዊትስ? - የዚህ ልዩነት ምክንያት ምንድነው?
6. አቢሣ ደጋግሞ እንዲበቀል ለዳዊት ቢመክረውም የዳዊትን እምቢ ማለት ስታይ ስለ ዳዊት ምን ታያለህ?
7. ዳዊት የሰደበውን ሊቀጣ ሲችል በይቅርታ ማለፉ ስለ ዳዊት ባህርይ ምን ያስረዳል?
   - በቁ. 22 "ዛሬስ ... "በማለት ሲናገር ዳዊት በዕለቱ የተረዳው ነገር ምንድነው?
8. ይህ ሁሉ በዳዊት የደረሰቐት ለምንድነው?
9. በችግርህ ላይ ችግርን ሊያመጣብህ የሚፈልግን ሰው ከመበቀልና ከመቀበል የት ው ይከብድሃል?
   - ይቅርታህ እስከየት ድረስ መዝለቅ አለበት?
   - ታላቁ ንጉስ በህዝቡና በሰራዊቱ ፊት ክብሩን የሚነካ ነገር ባጋጠመው ጊዜ ያደረገውን ስትመለከት የእግዚአብሔርን በጎነት መጠባበቅ የቱን ያህል መልካም መሆኑን ታያለህ?



መሪ ርዕስ ፦ "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.13፥22

- ዳዊት አብረውት ለነበሩት ሰዎች ሳያልን እንዳይበቀሉ እንደ ከለከላቸው ስታይ አንተስ ለምትመራቸው ሰዎች ምን አይነት ምሳሌነት ታሳየለህ? ሌላ ከዚህ ክፍል ያስተዋልከው ካለ ብታካፍል?

ማዛመድ

- በህይወት አስቸጋሪ ፈተና በሚገጥምህ ጊዜ እግዚአብሔርን በማሰብ ልብህን ታበረታለህ ወይስ ትጨነቃለህ?
- የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ምሪት በህይወት ምን ያህል አጥብቀህ ትፈልጋለህ
- በሰልፉ ሜዳ ለአሸናፊነት የሚያበቃህ ነገር የእግዚአብሔር ከአንተ ጋር መሆኑን እንጂ የሰራዊት ብዛት አለመሆኑን ከዚህ ክፍል ምን ያህል ተረዳህ?
- ዳዊት በተጨነቀ ጊዜ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር መለስ ህዝቡ ግን ዳዊትን የችግሩን ምክንያት ለመውገር ተነሳ አንተ ማን ውን ትመስላለህ?

## ጥናት 4

**ርዕስ፥ ልቡን በአምላኩ ያበረታው ዳዊት 1ሳሙ.30፥1-25**

ዓላማ፥ አማኝ በፊቱ ካለው ነገር የተነሳ ሳይረበሽ በእግዚአብሔር አምላክ ልቡን ቢያበረታ ጠላቱን ሊያሸንፍና ምርኮን ሊያገኝ እንደሚችል ለማሳየት

መግቢያ፥ እስራኤላውያንን ለመውጋት ዳዊት ከፍልስጤማውያን ጋር ለሰልፍ ቢወጣ የፍልስጤማውያን መኳንንት አብሮ መውጣቱን በመቃወማቸው ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ጥያቄዎች፥

1. ዳዊትና ሰዎቹ ወደ ጺግላግ በመጡ ጊዜ በሰፈራቸው ውስጥ ሆኖ ያገ -ት ነገር ምን ነበር?
   - ስለሆነው ነገር ዳዊትና ሰዎቹ ምን ተሰማቸው?
   - ለገጠማቸው ነገር የዳዊትና የሰዎቹን ምላሽ አወዳድር
2. ዳዊት በገጠመው አስጨናቂ ነገር ልቡን በእግዚአብሔር አምላኩ አበረታ ይላል። በዚህ ዳዊት ምን ምንን በማሰብ ይመስልሃል ልቡን ያበረታታው?
3. በአምላኩ ልቡን ያበረታው ዳዊት ምን ሊያደርግ ይታያል?



መሪ ርዕስ ፦ "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.13፥22

## ጥናት 10

**ርዕስ፥የንጉስ ይቅርታ 2ሳሙ.16፥5-11, 2ሳሙ፥19፥15-23**

ዓላማ፥ 1. አማኝ በመከራው ወቅት ችግሩን የሚያባብሱ ብዙ ሁኔታዎች ቢገጥሙትም እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ እንዳለበት ለማሳየት

2. አማኝ ለሚበድሉት ይቅርታን ማድረግ እንዳለበት ለማስገንዘብ

መግቢያ፥ ንጉሱ ዳዊት ልጁ አቤሰሎም በአመጽ በነገሰበት ጊዜ ያጋጠመውንና ያደረገውን ነገር እናያለን።

1. ሳማ የተባለው ሰው በዳዊት ላይ የሚናገረው ምንድነው? ምክንያቱስ?
   - ንጉሱ በሰራዊቱና በደጋፊኙ ፊት ሲሳደብ የሚመልሰውን መልስ ስታይ ምን ታስተውላለህ?
2. አቢሣ ምን ርምጃ ለመውሰድ ያስባል? ዳዊትስ ምን ይመልሳል?
3. ዳዊት የአቢሳን ምክር ያልተቀበለው ለምንድነው?
   - በቁ.11 ዳዊት ለእግዚአብሔር አዞታልና ብሎ ሲናገር ምን ማለቱ ነው?

5. **ዳዊት ከውድቀቱ ከተነሳ በኋላ ምን ማድረግ ያስባል? /ቁ.13/**
6. **ዳዊት እግዚአብሔር ደስ ስለቢሰኝበት ነገር ምን ይላል? ለምን?**

   **- ከዚህ አያይዞ ዳዊት ስለምን ይጸልያል?**

**ተዛምዶ**

**- ኃጢአትን መሰወር ጉዳት የሚያመጣ መሆኑን ስታይ ፈጥኖ ንሰሃ መግባት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስተዋልክ?**

**- ከእግዚአብሔር የምናገኘውን በረከት ኃጢአት እንደሚዘጋና የአዲስ ህይወትህም ትርጉም እንደሚያጠፋብህ ተረዳህ?**



መሪ ርዕስ ፡- “እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ” ሐዋ.13፥22

**- የእግዚአብሔርስ ምላሽ ምን ነበር?**

**- በዚህ ውስጥ ስለ ሁኔታው እግዚአብሔርን መጠየቅ ለመጨረሻው ውጤት ያለው ጥቅም ምንድነው?**

4. **ዳዊትና ሰዎቹ ጠላቶቻቸውን ለመያዝ በሄዱ ጊዜ በመንገድ ላይ የሆነውን ሁኔታ ዘርዝር? ቁ.9-15**

   **- በመንገድ ላይ ያገኙት ግብጻዊው ብላቴና መርቶ ወደ ጠላቶቻቸው ሰፈር በደረሱ ጊዜ የነበረው ሁኔታ እንዴት ነበር? ውጤቱስ?**
5. **እግዚአብሔር የመራውን ምችት እንዴት እንዳጸናው ታያለህ?**
6. **ጠላቶቻቸውን ባገኙት ምርኮ የተፈጠረው ችግርና ዳዊት ለዚህ የሰጠው መፍትሄ ምን ነበር?**

   **- ዳዊት ከሰልፍ በድካም የቀሩት ከሰልፈኞች እኩል ሊያገኙ ይገባል ሲል የተናገረበት ምክንያት ምን ነበር?**
7. **ዛሬ የተማርከውን አካፍል**

## ጥናት 5

**መሪ ርዕስ፥ "እግዚአብሔር ታቦት ፊት የዘፈነው ዳዊት" 2ሳሙ.6፥1-23**

ዓላማ፥ 1. አማኝ በሚኖረው ሕይወት ለእግዚአብሔር ሥፍራ ሲሰጥ እግዚአብሔር እንደሚባርከው ለማስገንዘብ

2. አማኝ በልብ ንጽህና በእግዚአብሔር ፊት ሲኖር ሳለ ሌሎች እንደ ሞኝነት እንደሚቆጥሩት ለማስገንዘብ

መግቢያ፥ ከሰያል ሞት በኋላ ዳዊት በመ- መሪያ በእስራኤል ንጉስ ላይ ንጉስ ሆነ ከዚህ በኋላ የእስራኤል አምላክ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ አገሩ ሲያገባ ያጋጠመውን ነገር እናያለን።

**ጥያቄዎች**

1. በክፍሉ መ- መሪያ ዳዊት ምን ሲያደርግ ይታያል?
   - የቃል ኪዳኑን ታቦት ሲይመጡ ያደረጉትን ነገር በዝርዝር ተናገር?
   - በቁጥር 5 ላይ "በሙሉ ኃይላቸው ይጫወቱ ነበር" ይላል ምን ማለቱ ይመስልሃል?



መሪ ርዕስ ፡- "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ
የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.13፡22

## ጥናት 9

**ርዕስ፥ የንሰሃ የተዋረደና የተሰባበር ልብ መዝ.51፥1-19**

ዓላማ፥ 1. በደለ የሆነ ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ማመጹን ለማሳየት

2. ራሱን አዋርዶ ንሰሃ የገባ መታደስን እንደሚያገኝ ለማሳየት

መግቢያ፥ ንጉሱ ዳዊት በኃጢአት ከወደቀ በኋላ እግዚአብሔር በነቢዩ ዮናታን በኩል ኃጢአት መስራቱን ከተናገረው በኋላ የገባውን ንሰሃ እንመለከታለን።

ጥያቄዎች

1. ዳዊት ስለመተላለፉ መደምሰስ ሲለምን የጠቀሳቸው የእግዚአብሔር ባህርያት ምንድን ናቸው?
   - መጠቀሳቸውስ ለምን አስፈለገ?
2. ዳዊት ስለኃጢአት ያለው አጠቃላይ መረዳት ምን ይመስላል?
   - በህይወቱ ያደረሰው ጉዳት ምንድነው? /8/
3. በቁ.5 እና 6 ስለ ሰውና ስለ እግዚአብሔር ያለው መረዳት ምንድነው?
4. ዳዊት እግዚአብሔር ምን ምን እንዲያደርግለተ ይለምናል?

4. የእግዚአብሔር ፍርድስ ምን ነበር? ይህስ ስለ እግዚአብሔር ባህርይ ምን ያሳያል?
   - እርሱን በአሞን ልጆች ሰይፍ ገድለሃል ያለው ስለምንድነው?
5. በዚህስ ከእግዚአብሔር ጠላቶች ጋር እንዴት ሲተባበር ይታያል? - ይህስ ስለ ኃጢአት ምን እንድታስተውል ያደርግሃል?
6. ዮናታንን መልዕክት ዳዊት እንዴት ተቀበለ? ምንስ ሊያደርግ ይችል ነበር?
   - ከዚህስ ስለ ዳዊት ባህርይ ምን ትረዳለህ?
7. ኃጢአት በሰሪው ብቻ ተወስኖ የማይቀረው ለምንድነው? /ቁ. 14/
   - ልጁ በተቀሰፈ ጊዜ ዳዊት በምን ሁኔታ በእግዚአብሔር ፊት ቆየ? ለምን? ይህስ ስለ ዳዊት ምን ያስረዳሃል?
8. ለዳዊት የተወለደው ህጻን ሲሞት ዳዊት ያደረጋቸውን በየቅደም ተከተላቸው ግለጽና ከዚህ ስለ ዳዊት የምትረዳውን ተናገር? - በህጻኑ ሞት ሰዎች ስለ ዳዊት የነበራቸውን ግምትና የዳዊት ሁኔታ ልዩነት ከምን የተነሳ ይመስልሃል?
9. ስለ እውነተ ንስሃ ከክፍሉ ምን ትረዳለህ?

- ለእግዚአብሔር ተግሳጽና ምክር ምን አይነት ልብ ሊኖርህ እንደሚገባ አየህ?



መሪ ርዕስ ፡- "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.13፥22

2. የእግዚአብሔርን ታቦት እያመጡ ሳሉ በበሬዎች መፋነን ታቦቱን ለያዘው ያጋጠመው ነገር ምን ነበር?
   - ዳዊት በዚህ የያዛ ሞት ምን ሲሰማውና ምን ሲያደርግ ይታያል?
3. እግዚአብሔር ያዛን የቀሰፈው ስለምን ነበር?
   - ከዚህ አደራረጉ እግዚአብሔር ለዳዊትም ሆነ ለእስራኤል ምን ሊያስተምር ነው የፈለገው? ዘኍ.4፥15, 1ዜና.15፥13-15
4. ከሆነው ነገር የተነሳ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት ወዴት ሲወስደው ይታያል?
   - በአቢዳራ ቤት ታቦቱ በመቀመጡ እግዚአብሔር እሱንና ቤቱን /ቤተሰቡን/ መባረኩን ስታይ ምን የምታስተውለው ነገር አለ?
5. ንጉሱ እግዚአብሔር የአቢዳራን ቤት መባረኩን በሰማ ጊዜ ያደረገው ምን ነበር?
   - ለደስታቸው ዋና ምክንያት የሆነው ነገር ምን ነበር? ከዚህስ ምን ታስተውላለህ?
6. የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ ካመጡ በኋላ የሆነው ነገርን በዝርዝር ተናገር? ቁ.16-22
7. በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ዳዊት እንደዚያ ባለ መንገድ መጫወቱን ያየችው ሜልኮል ስለ ዳዊት የሰጠችው አስተያየት ምን ነበረ?

- ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ የሚያስፈልገው ነገር በፈቃደኝነት በመስጠት የሚያገ ውን ሰማያዊ ደስታ በህይወትህ ምን ያህል እየተለማመድከው ነው?
- የእግዚአብሔር ሥራ በፍቅርና በአክብሮት ትሠራለህ? ወይስ በመሰልቸት?
- ከክፍል ስለ ራስህ ትምህርት ሊሆን የሚችል የዳዊት ባህርይ ምን አስተዋልክ?



መሪ ርዕስ ፡- "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.13፥22

## ጥናት 8

**ርዕስ፥የታላቁ ሰው ታላቅ ኃጢአት ቅጣት**

**2ሳሙ.12፥1-23**

ዓላማ፥ 1. በኃጢአት የወደቀው ሰው ለመነሳት ሊወስዳቸው የሚገባው ርምጃ ለመመልከት

2. በንስኃ ወደ እግዚአብሔር የተመለሰ ሰው /የቀረበ/ በህወቱ ታድሶ መመላለስ እንደሚችል ለማሳየት

መግቢያ፥ ዳዊት ከወደቀበት ለመነሳት የወሰደውን የንሰሃ ርምጃና እግዚአብሔር እንደገ በምህረቱ ሲመልሰው የሚያሳያውን ክፍል እናጠናለን።

ጥያቄዎች፥

1. እግዚአብሔር በነቢዩ በናታን ዳዊትን ለመመለስ የተጠቀመበት ዘዴ ምን ነበር?
   - ለምን ይህን ዘዴ ተጠቀመ?
2. የዳዊት መልስ ምን ነበር? - ከዚህስ በአጠቃላይ ስለ ለሰዎች ባህርይ ምን ትረዳለህ?
3. ዳዊት የወደቀበትን ኃጢአት እንዳይሰራ ሊገነዘበው የሚገባ ነገር ምን ነበር?

ርምጃዎች ሲወስድ ትመለከታለህ?

4. ዳዊት ደረጃ በደረጃ ስህተቱን ለመሸፈን የወሰዳቸውም ርምጃዎች መልካም ውጤት አስገ ኙለትን? ለምን? /ቁ.27 ተመልከት/

   - ዳዊት ስህተቱን ለመሸፈን ሲል ለኦርዮ የሚሰጠውን ትዕዛዝና የኦርዮንን መልስ ስታወዳድር ከሁለቱ ባህርይ ምን ታስተውላለህ?

   - ዳዊት ስህተቱን ለመሸፈን ሲል በኦርዮን ላይ በጦር ሜዳ የሚያስወስደው ርምጃ በህዝቡ ድል ላይ ምን አይነት ውጤት አስከተለ?

5. ዳዊት በመጨረሻ ምን ርምጃ ይወስዳል?
6. ዳዊት ደረጃ በደረጃ በመውደቁ እግዚአብሔር ለህዝቡ የሰጠውን ስንት ትዕዛዝ ሲያፈርስ ታያለህ? /ዘጸ.20፥13-17/
7. ስህተትን በሌላ ስህተት ለመሸፈን የማይቻለው ለምን እንደሆነ ትረዳለህ?

<u>ተዛምዶ፥</u>

- ከውድቀት ለመጠበቅ ምን ዓይነት ጥንቃቄና እርምጃ መውሰድ እንዳለብህ ትገነዘባለህ?
- ኃጢአትን በኃጢአት መሸፈን እንደማይቻል ስታስታውስ ለአንተ ምን ትምህርት ይሰጥሃል?
- ከክፍሉ በተለይ መንገድ ለራስህ የምትማረው ቁም ነገር ካለህ አካፍል።





## <u>ጥናት 6</u>

### <u>ርዕስ፥ ዳዊት ለእግዚአብሔር ክብር ያለው አመለካከት</u>

<u>2ሳሙ.7፥1-27</u>

ዓላማ፥ - አማኝ ዕረፍትን ለሰጠው ለአምላኩ ቤት የሚቀና ሲሆን እግዚአብሔር እንደሚባርከው ለማስገንዘብ

⌖ አማኝ እግዚአብሔር ከዋለለት ውለታ የተነሳ በማስተዋልና በመረዳት ለእግዚአብሔር ክብር ሊኖራቸው የሚገባውን አመለካከት ለማስገንዘብ

መግቢያ፥ ንጉሥ ዳዊት እርሱ ያለበትን የኑሮ ሁኔታና የእግዚአብሔር ታቦት ያለበትን ሁኔታ በማገናዘብ ለእግዚአብሔር ሊያደርግና ሊሠራ ያሰበውን እንመለከታለን።

ጥያቄዎች፥

1. ዳዊት የእግዚአብሔር ታቦት ያለበትን ሁኔታና የእርሱን የኑሮ ሁኔታ ሲያይ ምን ሊያደርግ ያስባል።

- ይህንን ለማድረግ ያሰበው በምን ሁኔታ ላይ ሆኖ ነው?
- በዚህ ሁኔታ ላይ ሆኖ ይህን ማሰቡን ስታይ ስለ

ዳዊት ባህርይ ምን ትረዳለህ?

2. ለዳዊት ፍላጎት ዮናታንና የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ነበር?
3. ለዳዊት ፍላጎት የእግዚአብሔርን ምላሽ በዝርዝር ስትመለከት እግዚአብሔር የዳዊትን መሻት /አመለካከት/ ያቃለለ ይመስልሃል? ለምን?
4. ዳዊት ባሳየው የልብ ቅንነት እግዚአብሔር ለራሱ, ለመንግስቱ, ለልጆቹና ለህዝቡ ሊያደርግ የሚገባውን ቃል ስትመለከት የአንድ ሰው /መሪ/ መታዘዝ የሚያመጣውን ባርኮት የቱን ያህል መሆኑን ታያለህ?
5. ለዚህ ለእግዚአብሔር ተስፋና ቃል የዳዊት ምላሽ ምን ነበር?

   - በጸሎቱ ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ባህርይ የሚጠቅሳቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?
6. መቁ.27 ላይ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤት ለመስራት ሲያስብ እግዚአብሔር እኔ ቤት እሰራለሁ ብሎ ሲናገረው ከዚህ የምትረዳው ምንድነው?

   - እግዚአብሔር ስለ ተናገረው ነገር ዳዊት ለየት አድርጎ የሚናገረው ነገር ምንድነው?
7. ለእግዚአብሔር ክብር ያለን አመለካከት ሊያመጣ የሚችለው ውጤት ምን እንደሆነ ታያለህ? - ለእግዚአብሔር ቤትን ሊሰሩ ለሚያስቡ እርሱ ቤት እንደሚሰራላቸው ስታይ ምን ትረዳለህ?

   - በአጠቃላይ ከዚህ ክፍል ምን አስተዋልክ?



መሪ ርዕስ ፡- “እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ” ሐዋ.13፡22

## ጥናት 7

### ርዕስ፥ የታላቅ ሰው ታላቅ ውድቀት 2ሳሙ.11፡1-27

ዓላማ፥ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው እንኳን በማስተዋል ካልተመላለሰ በቀላሉ ለውድቀት ሊጋለጥ እንደሚችል ለማሳየት

- ከወደቁ በኋላ ስህተትን በትክክለ የእግዚአብሔር መንገድ አለማረም የባሰ ውድቀት ጥፋትና እንደሚያስከትል ለማሳየት

መግቢያ፥ ዳዊት ምንም እንኳን የተመሰከረቃት ለእግዚአብሔር የልብ ሰው ቢሆንም በህይወቱ
ገጥሞት የነበረውን ታላቅ ውድቀትና የውድቀቱን መንሥዔ በዛሬው ጥናት እናያለን።

ጥያቄዎች

1. በታሪኩ በመግቢያ ላይ ዳዊት ምን ሲያደርግ እንመለከታለን?
2. እርሱስ የት ነበር? ምንስ ገጠመው?

   - በዚህ ሁኔታ እንዳይወሰድ ዳዊት ምን ማድረግ ነበረበት ትላለህ?
3. ሴቲቱ ማርገዝዋን ስትነግረው ዳዊት ምን ምን